የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ታህሳስ 22/2001

## ሰብዓዊ መብት በግማሽ የሚል ፈሊጥ የለም

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በግፍ የታሰሩ ዜጎችን ጉዳይ አንስቶ በአስቸኳይእንዲፈቱ በሚጠይቅበት ጊዜ ከአንዳንድ ክፍሎች ሂስ ሲቀርብበት ቆይቷል፡፡ የታሰረው ግለሰብ በፖለቲካ አቅዋሙ ወይም ታሪኩ የሚጠሉት እንኳን ታሰረ ይሉና ኮሚቴውም ዝም እንዲል ይጠይቃሉ፡፡ በግማሽ ወይ በፖለቲካ ወገንተኝነት ተነስቶ የሰብዓዊ መብትን ጉዳይ ማየት ተገቢ አለመሆኑን ኢፖእአኮ መግለፅ ይገደዳል፡፡

ኢፖእአኮ በኢሠመጉ ላይ ያለው ዋና ወቀሳ፤ በአምኔስቲ ኢንተርናሽናልና በሀዩማን ራይትስ ዋች ዓይነቶቹ ተቋሞች ላይ ያለው ዋነኛ ወቀሳ ይህ በፖለቲካ የተንሸዋረረ አቅዋም አንዳንድ እስረኞችን ስማቸውን እንዳያነሱ በማድረጉ ነው፡፡ ለምሳሌ የኢሕአፓ መሪዎችና ነባር አባሎች ተይዘው ደብዛቸው መጥፋቱ እየታወቀ ኢሠመጉ ምንም ጊዜ ቢሆን ስለነሱ ዘግቦ አያወቅም፡፡ አምኔስቲና ሀዩማን ራይትስ ዋችም ቢሆኑ በድርጅቱ ላይ የከረመ መጥፎ አቅዋም ስላላቸው ደብዛቸው የጠፉ ብለው የኦነግ አባላትን በተደጋጋሚ ሲያቀርቡ ስለ ኢሕአፓ ግን ትንፍሽ ብለው አያውቁም፡፡ የብሄረሰብ ድርጅቶችም ቢሆኑ ከራሳቸው አባላትና ደጋፊ ውጭ ስለሚታሰሩ ኢትዮጵያውያን አንዳችም መስመር ካለመፃፋቸው አልፎ መያዛቸውንም ለመካድ ይዳዳቸዋል፡ አምኔስቲ የአቶ አበራ የማነአብን ህገወጥ እስር በተመለከተ ወያኔ የሚሰጠውን ምክንያት በመደገፍ የአቶ አበራን ጉዳይ አንስቶ አያውቅም፡፡ አምኔስቲ በኢትዮጵያ የሚደርሰውንም የመብት ረገጣ በብሄረሰብ አድልዎ ይዞ እየተጓዘ ስለ አንዱ መጠቃት ሲያወሳ ስለሌሎች ግን ጆሮ ዳባ ልበስ ማለቱ የሚታወቅ ነው፡፡ኢፖእአኮ በአንፃሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ዜጋ በህገወጥ መንገድ መብቱ ሲደፈር ከመጮህና ለመቃወም ወደኋላ አላለም፡፡ ስዬ አብርሃና ታምራት ላይኔ ለምሳሌ የዚሁ አፋኝ አገዛዝ አካል የነበሩ ቢሆኑም የታሰሩት በህግ ስላልነበር ተቃውሟል፡፡ ወያኔ በሶማሊያ ገብቶ የፈፀመውን የመብት ረገጣ እንዳጋለጠው ሁሉ አክራሪዎቹ አል ሸባቦችም የወሰዷቸው ን ኢሰብዓዊ እርምጃዎች ኮንኗል፡፡ በኡጋዴንም እንዲሁ፡፡

ሰብዓዊ መብት ሙሉ በሙሉ ለሁሉም መከበር አለበት፡፡ ሰብዓዊ መብት አስከባሪ ኮሚቴዎች ወይም ተቋሞች ፖለቲካዊ አቅዋም ሊኖራቸው ወይም የፖለቲካ ዝንባሌያቸው የሰብዓዊ መብት ስራቸውን ሊቃኝ አይገባውም፡፡ ሰብዓዊ መብትም ለነጮች ወይ ሰለጠኑ ለተባሉት ብቻ እንጂ ለአፍሪካውያን ተሸራርፎ ነው መድረስ ያለበት የሚለውንም ዘረኛ አቅዋም ኢፖእአኮ አይቀበለውም፡፡ በፆታ፤በዘር፤ በቀለም፤ በፖለቲካና ህይማኖት የተነሳ የሚደረግ ልዩነትን ሁሉ የት ቢሆን የት መቸም ቢሆን ይቃወማል፡፡ ማንም ቢሆን ማን ያለው/ ያላት የፖለቲካ አቅዋም የራሱ/የራሷ መብት/መብቷ ሲሆን ህገወጥ በሆነ መንገድ መያዙን/መያዟን መቃወም ግን የግድ ነው፡፡ ታምራት ተፈታ ስንል አበራም ይፈታ ብሎ መጠየቅ፤ እገሌ ጋዜጠኛ ተያዘ ጠፋ ሲባል እነ ብርሀኑ እጅጉስ ማለት፤ በኦጋዴን እየደረሰ ያለውን ስንቃወም በሌሎች ቦታዎችም በሕዝብ ላይ የሚደርስውን በደል ማጋለጥ፥ የእገሌ ድርጅት አባላት ታስረው ደብዛቸው ጠፋ ስንል የኢሕአፓዎቹስ ብሎ መጮህ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ካለውና ከሰፈነው የተለየ አቅዋም ያላቸው ወይም ውሁዳን የሆኑ መብት ሊነፈጉ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ኢፖእአኮ ሰብዓዊ መብትን በሁለገብ ገፅታው እየወሰደ የፖለቲካ አቅዋምና ዝንባሌ መቆሮቆርና መጮህ ያለብንን ሊያግደን ሊያስቆመን አይገባም ይላል፡፡

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE